የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ ጥር ፴ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No.20
ADDIS ABABA 7th February, 2005

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፭/፲፱፻፺፯ ዓ.ም**

ለአዘዞ መተማ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኤኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ....ገጽ... ፫ሺ፴፭

**CONTENTS**

**Proclamation No. 435/2005**

Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for financing the Azezo Metema Road Project Ratification Proclamation No. Page 3035

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፭/፲፱፻፺፯

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኤኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአዘዞ-መተማ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፲፫ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አሥራ ሶስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፳፫ ፪ሺ፬ በካርቱም የተፈረመ በመሆኑ፣

መሠረታዊ የኤኮኖሚ ዓለም ዐቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መፅደቅ ስላለባቸው፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሣሥ 28 ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለአዘዞ-መተማ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኤኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፬፻፴፭/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

## PROCLAMATION NO. 435/2005.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of thirteen million United States Dollars (USD 13,000,000) for financing the Azezo Metema Road Project;

**WHEREAS,** basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Credit Agreement at its session held on the 6th day of January, 2005;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for financing the Azezo Metema Road Project Ratification Proclamation No. 435/2005."

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኤኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ኦክቶበር ፳፫ ቀን ፪ሺ፬ በካርቱም የተፈረመው የብድር ስምምነት ነው::

## ፫. የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፫ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አሥራ ሶስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል::

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር ፴ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ጥር ፴ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## 2. Definition

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement signed between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa on the 23rd day of October, 2004.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of thirteen million United States Dollars (USD 13,000,000),000) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force as of 7th day of February, 2005.

**Done at Addis Ababa, this 7th day of February, 2005.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት